# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መግቢያ

## ክፍል ፩

«የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ» /ቆላ.3÷16/

አዘጋጅ፡- ዲ/ን ዘላለም ቻላቸው



«አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነስቷል፡፡ ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ በክርስቶስ ደግሞ ህያዋን ይሆናሉና፡፡» 1ኛ ቆሮ. 15፥20-21



«እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ብርቱ የሆነ በእርሱ ለእኔ ታላቅ ሥራን አድርጓልና፡፡» ሉቃ. 1፥49

# ማውጫ

መቅድም........................................................................................ 1

1. መግቢያ

1.1. መጽሐፍ ቅዱስ ምንድን ነው? ................................................ 2

1.1.1. ሰዋስዋዊ /የቁም ፍች........................................................ 2

1.1.2. ዐውዳዊ ፍች.................................................................... 2

1.1.3. የቃላት አጠቃቀም ........................................................ 3

1.2. ለምን ቅዱስ ተባለ?.................................................................. 3

1.3. የመጽሐፍ ቅዱስ ባሕርያት........................................................ 4

1.4. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሞች ........................................................ 8

1.5. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መርሆዎች........................................... 11

1.6. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አጠቃላይ መመሪያዎች ..................... 13

1.6.1. ዝግጅት ማድረግ ............................................................ 13

1.6.2. በመገዛት፣ በማድነቅና በትሕትና ማንበብ ....................... 15

1.6.3. ትክክለኛውን ትርጉም ለመረዳት መጣር ........................ 16

1.6.4. ለሕይወት ማንበብ........................................................... 18

# መቅድም

መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው ልጆች የእምነትና የሕይወት መመሪያ እንዲሆን ከእግዚአብሔር የተሰጠ መጽሐፍ ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሚናገርባቸው መንገዶችም አንዱ ነው። በትክክል ያነበቡትን፣ የተረዱትንና የተመሩበትን ሰዎችም መንገዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲያደርጉ አስችሏቸዋል /ረድቷቸዋል/።

በዘመናችን መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብን በተመለከተ ሁለት ዐበይት ችግሮች ይስተዋላሉ።

1. ብዙ ምዕመናን መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የተሰጠ መጽሐፍ እንደሆነ ከማመንና መጽሐፍ ቅዱስን ከማክበር አልፈው መጽሐፍ ቅዱስን ሲያነቡ አይስተዋሉም። በዚህም ምክንያት ከመጽሐፉ ሊያገኙት የሚገባቸው ብዙ ጥቅም ቀርቶባቸዋል።

2. ሌሎች ደግሞ ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስን ቢያነቡም እንዴት መነበብና መጠናት እንዳለበት ባለመረዳታቸው ለጥርጥርና ለክህደት ይደረጋሉ።

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ለእነዚህ ሁለት ችግሮች መፍትሔ እንዲሰጥ ማለትም ለሰው ልጆች የሕይወት እና የእምነት መመሪያ እንዲሆን የተሰጠውን መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ማንበብ እንዳለብን የሚናገር መመሪያ እንዲሆን ነው።

ምጽሐፉ ዐራት ዋና ክፍሎች አሉት። በመጀመሪያው ክፍል የመጽሐፍ ቅዱስን ምንነት ባሕርያት ጥቅም እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መርሖዎችን እንመለከታለን።

በሁለተኛው ክፍል የመጽሐፍ ቅዱስን አጠቃላይ ይዘትና ክፍሎች እንዳስሳለን።

በሦስተኛው ክፍል መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብና ለመረዳት ሊታወቁ የሚገባቸውን የመጻሕፍቱን በእግዚአብሔር መንፈስ መጻፍ እና ቀኖና የመሳሰሉ ነገሮች እናያለን።

በዐራተኛው ክፍል መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ በዚያ መጽሐፍ ያለውን የእግዚአበሔር መልእክት በትክክል ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት መጠናት እንዳለበት ይህንን ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ የጥናት ስልቶችን እንመለከታለን።

# <u>ክፍል አንድ</u>

# <u>መግቢያ</u>

## 1.1 መጽሐፍ ቅዱስ ምንድን ነው?

### 1.1.1. ሰዋሰዋዊ /የቁም/ ፍቺ

«መጽሐፍ ቅዱስ» የሚለው ሐረግ[1] ግእዝ ሲሆን በአማርኛ «ቅዱስ መጽሐፍ» ማለት ነው:: ሐረጉ የተመሠረተባቸው ሁለት ቃላት ትርጉም እንደሚከተለው ነው::[2]

<u>መጽሐፍ</u>፡- በላዩ ላይ ነገር የተጻፈበት ብራና፣ ወረቀት፣ ነዶው በአንድነት የታሰረና የተያዘ የተሰፋ የተጠረዘ ጽሑፍ ማለት ነው::

<u>ቅዱስ</u>፡- ክቡር፣ ምስጉን፣ ልዩ፣ ምርጥ፣ ንጹሕ፣ ጽሩይ ማለት ነው::

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ማለት በቁሙ የተከበረ፣ የተለየ፣ ንጹህ የሆኑ ጽሑፎች ስብስብ፤ ጥራዝ ማለት ነው::

### 1.1.2. ዐውዳዊ ፍቺ

በዚህ ጽሑፍ የምንናገርለትን መጽሐፍ ለመግለጽ ጥቅም ላይ ሲውል «መጽሐፍ ቅዱስ» የሚለው ሐረግ ሁለት ተያያዥነት ያላቸው ትርጉሞች አሉት::

በተለያዩ ዘመናት የተነሱ ቅዱሳን ሰዎች የእግዚአብሔርን ማንነት፣ ባሕርያት፣ ሥራዎች፣ ከሰው ልጆች ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲሁም የሰው ልጆችን ለማዳን በባሕርይ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የተከናወኑትን ነገሮች የሚገልጹና ለሰው ልጆችም የሕይወት መመሪያ የሚሆኑ በርካታ መጻሕፍትን ጽፈዋል:: ከእነዚህ መጻሕፍት መካከል የተወሰኑት በቤተ ክርስቲያን ጉባኤያት እና አባቶች ተለይተው /ተመርጠው/ እና በቁጥር ተወስነው አሥራው መጻሕፍት ተብለው ይጠራሉ::[3] እነዚህ መጻሕፍትም ኦሪት ዘፍጥረትን፤ ኦሪት ዘጸአትን፣ መጻሕፍተ ነገሥትን፣ የትንቢት መጻሕፍትን፣ አራቱን ወንጌላትን /የማቴዎስ፤ የማርቆስ፣ የሉቃስና የዮሐንስ/፤ . . . የተለያዩ ሐዋርያት መልእክታትንና የዮሐንስ ራእይን የመሳሰሉት መጻሕፍት ናቸው::[4]

---

1. አለቃ ኪዳነ ወልደ ክፍሌ፣
2. ሐረግ ማለት ከሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ቃላት በማጣመር የሚፈጠር ቃል ማለት ነው::
3. ስለ አሥራው መጻሕፍት እና ስለቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና በስፋት በክፍል ሦስት እንመለከታለን::
4. የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክርስቲያን የምትቀበላቸው አሥራው መጻሕፍት ዝርዝር በክፍል ሁለትና ሦስት እንመለከታለን::

እንግዲህ «መጽሐፍ ቅዱስ» የሚለው ሐረግ

ሀ. እነዚህን መጻሕፍት /ሁሉም ወይም በከፊል/ በአንድነት የሚገኙበትን መጽሐፍ /የመጻሕፍት ጥራዝ/

ለ. መጻሕፍቱን እያንዳንዳቸውን ይወክላል።

### *1.1.3 የቃላት አጠቃቀም*

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ቃላትን በሚከተለው መልኩ እንጠቀማለን፤

መጻሕፍቱን እያንዳንዳቸውን /በተናጠል/ ለመጥቀስ ሲፈለግ የመጻሕፍቱን ልዩ ስም እንጠቀማለን። ለምሳሌ የኦሪት ዘፀአት መጽሐፍ፣ የትንቢተ ኢሳይያስ መጽሐፍ፣ የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ፣ የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ወዘተ . . . እንላለን።

መጻሕፍቱን በጥቅል ለመጥቀስ ሲፈለግ «ቅዱሳት[4] መጻሕፍት» እንላለን። ለምሳሌ «ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ» ስንል መጽሐፍ ቅዱስ በሚባለው የመጻሕፍት ጥራዝ /ስብስብ/ ውስጥ የተካተቱን የተለያዩ መጻሕፍት ማንበብ ማለት ነው።

ሁሉንም መጻሕፍት እንደ አንድ የተጠረዘ መጽሐፍ ለመጥቀስ ሲፈለግ ደግሞ መጻሕፍቱን የያዘውን ጥራዝ «መጽሐፍ ቅዱስ» ብለን እንጠራዋለን።

በመጻሕፍቱ ውስጥ ያለውን ቃል /ምንባብ/ /የመጻሕፍቱን ይዘት/ ደግሞ «ቃለ እግዚአብሔር እንለዋለን። ለምሳሌ «ቃለ እግዚአብሔር የነፍስ ምግብ ነው» ስንል «በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈ ቃላት /ምንባባት/ የነፍስ ምግቦች ናቸው፤ ለነፍስ ጤናማ ሆኖ መኖር አስፈላጊ ናቸው» ማለታችን ነው። ቃለ እግዚአብሔር መባላቸውም ወደፊት እንደምንመለከተው የመጻሕፍቱ አስገኚ እና ባለቤት ልዑል እግዚአብሔር በመሆኑ ነው።

## 1.2 ለምን ቅዱስ ተባለ /ተባሉ/?

«መጽሐፍ ቅዱስ» የሚለውን ቃል ሰዋስዋዊ /የቁም/ ፍቺ ስናይ ቅዱስ ማለት «ክቡር፣ ምስጉን፣ ልዩ፣ ምርጥ፣ ንጹሕ፣ ጽሩይ» ማለት መሆኑን ተመልክተናል። በዚህ ርዕስ የምንመልሰው ጥያቄ «በዚህ መጽሐፍ እየተነጋገርንበት ነው ያለውነን መጽሐፍ /መጽሐፍ ቅዱስን/ ቅዱስ ያደረገው ምንድን ነው? የሚለውን ነው።»

---

4. «ቅዱሳት» የ«ቅዱስ» ብዙ ቁጥር /በአንስታይ ጾታ/ ነው።

በአጭሩ መጽሐፍቱ ቅዱስ /የሆኑት/ አስገኛቸው ቅዱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

«ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፉ ናቸው። ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማነጽ በጽድቅም ላለው ጥበብ ሁሉ ይጠቅማሉ።» /፪ኛ ጢሞ. ፫፥፲፮/

«. . . ትንቢት ከቶ ከሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተረድተው ተናገሩ» /፪ኛ ጴጥ. ፩፥፳ - ፳፩/

«አንድ የመጽሐፊ ክርታስ ውስድ ለአንተም ከተናገርኩበት ቀን .. . ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በእሥራኤልና በይሁዳ ላይ በአሕዛብም ላይ የተናገርሁህን ቃል ሁሉ ጻፍበት» /ኤር. 36.2/

ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት በቅዱስ እግዚአብሔር ፈቃድ፣ አነሣሽነት፣ ረዳትነት፣ ጠባቂነት /ከስህተት/፣ ገላጭነት የተጻፉ ስለሆኑ ቅዱሳት ናቸው፤ «ቅዱሳት መጻሕፍት» ይባላሉ። መጻሕፍቱ በአንድ ላይ የሚገኙበት ጥራዝም /መጽሐፍም/ «መጽሐፍ ቅዱስ» /«ቅዱስ መጽሐፍ»/ ይባላል።

## 1.3 የመጽሐፍ ቅዱስ ባሕርያት

የመጽሐፍ ቅዱስ ባሕርያት የምንላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ መገለጫ የሆኑትና መጽሐፍ ቅዱስን ከሌሎች መጻሕፍት ልዩ የሚያደርጉትን ነገሮች ነው። የእነዚህ ባሕርያት ምንጭ የመጽሐፉ /የመጻሕፍቱ/ አስገኚ እግዚአብሔር መሆኑ ነው።

### *ሀ. ዘመን እና ቦታ አይሽረውም /አይለውጠውም/*

ጽሕፈት ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ጸሐፊዎች በተለያዩ ዘመናት የተለያዩ መጻሕፍትን ጽፈዋል። እነዚህ መጻሕፍት በየዘመናቸው የብዙዎችን ቀልብ ስበዋል፣ ተወዳጅነትንና ታዋቂነትን አትርፈዋል። ሁሉንም ግን ዘመን ሽሯቸው ዛሬ በቦታቸው ሌሎች ተተክተዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከ3500 ዓመታት በፊት ጀምሮ የተጻፉት መጻሕፍትን የያዘ ቢሆንም ቅዱሳት መጻሕፍትን ዛሬም ሕያው ነው። የመጻሕፍቱ አስገኚ ሕያው የሆነው

አምላክ ስለሆነ በፊት በነበረው ዛሬም ላለው ለሚመጣውም ትውልድ የሚሆን መልዕክት አላቸው:: ስለዚህ ዘወትር ሕያው ናቸው::

ከዚህም በተጨማሪ መጻሕፍቱ መጀመሪያ የተጻፉት በ3 ቋንቋዎች /እብራይስጥ፣ ግሪክ እና አራማይክ/ ብቻ ቢሆንም ዛሬ መጽሐፍ ቅዱስ በበርካታ ቋንቋዎች ተተርጉሞ በመላው ዓለም ተሰራጭቷል::

## ለ. *ያለፈውንና የሚመጣውን በእርግጠኝነት ይናገራል*

አምላካችን እግዚአብሔር ቅዱሳት መጻሕፍትን ለጻፉ ሰዎች ከሰጣቸው ጸጋዎች መካከል ኃብተ ትንቢት አንዱ ነው:: ኃብተ ትንቢት ማለት ያለፉትን ነገሮች /ኃላፍያትን/ እና ወደ ፊት የሚመጡትን /መጻእያትን/፤ የማወቅ ስጦታ ማለት ነው::

በዚህም ምክንያት ጸሐፍቱ ከነበሩበት ዘመን በፊት የተከናወኑ ነገሮችን እርግጠ ኝነት ተናግረዋል::

ለምሳሌ ሙሴ እርሱ ከነበረበት ዘመን ከበርካታ ሺህ ዓመታት በፊት የሆነውን የዓለም መፈጠር በዝርዝር ጽፏል::

በርካታ ነቢያትም በየዘመናቱ እየተነሱ ወደ ፊት ስለሚሆኑና ስለሚደረጉ ነገሮች ተናግረዋል:: ነቢዩ ኢሳይያስ ከጌታችን መወለድ ብዙ ዓመታት አስቀድሞ የእመቤታችንን በድንግልና መጽነስና ወንድ ልጅ /ጌታችንን / መውለድ እንዲህ ሲል ተንብዮ ነበር:: «ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች፣ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፣ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች::» ኢሳ. ፯፥፲፬

ነቢዩ ዳዊትም ከጌታችን መወለድ 1000 ዓመታት ያህል አስቀድሞ የጌታችንን ሞትን ድል አድርጎ መነሣት እንዲሁም ወደ ሰማይ ማረግ /መውጣት/ እንደተፈፀሙ ሆነው አይቷቸው እንዲህ ሲል ተናግሮው ነበር::

«እግዚአብሔር ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፣» /መዝ. 77.65/

«እግዚአብሔር በእልልታና በምስጋና ዐረገ፣» /መዝ. 46.5/

ገና ወደፊት ስለሚረጉትና ስለሚሆኑት ነገሮችም የተነገሩ በርካታ ትንቢቶች አሉ ሌሎቹ ትንቢቶች እንደተፈፀሙት እነዚህም ደግሞ ጊዜያቸውን እየጠበቁ ይፈፀማሉ::

ከነዚህም በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች መጻሕፍት ተለይቶ በዓይነ ሥጋ ስለሚታየው ብቻ ሳይሆን ስለማይታየውም ዓለም ማለትም ልናያቸው ስለማንችላቸው ስለ ገነት፣ ሲኦል፣ መንግሥተ ሰማያት፣ መላእክት ስለ ሰማያዊቷ የእግዚአብሔር መንግሥት እና ስለመሳሰሉት ይናገራል።

## *ሐ. የሚሰሙትን ወደ ቅድስና ሕይወት ይመራል፣ ይባርካልም*

ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት በእግዚአዘብሔር መንፈስ ስለሆነ በውስጣቸው ያሉ ምንባባት የሰው ልብ ለእግዚአብሔር ፈቃድ የማስገዛትና ሰዎች በእግዚአብሔር መንገድ እንዲሄዱ የማድረግ ኀይል አላቸው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአይሁድ ተላልፎ ተሰጥቶ በተሰቀለ ጊዜ ከደቀመዛሙርቱ መካከል ሁለቱ /ሉቃስና ቀለዮጳ/ ይባላሉ። አስቀደሞ ስለ ትንሣኤው የሰጠውን ተስፋ ልብ ባለማለታቸው ተስፋ ቆርጠው ከኢየሩሳሌም ወጥተው መሄድ ሲጀምሩ ክብር ይግባውና ጌታችን በመካከላቸው ተገኝቶ አብሯቸው መጓዝ ጀመረ። በመንገድ ላይ ሳሉም ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጎመላቸው። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን እነርሱ አላወቁትም ነበር።

ወደሚሄዱበት መንደር ሲደረሱም ሊመሽ ጀምሯልና አብረኸን እደር ብለው ግድ ስላሉት አብሯቸው ወደ ቤት ገባ። በማዕድ ተቀምጠው ሳለም እንጀራውን ቆርሶ ሲሰጣቸው ዓይናቸው ተከፈተና አወቁት፣ እርሱም ከእነርሱ ተሰወረ። ከዚህ በኋላ እርስ በእርሳቸው እንዲህ ተባለለ፣

«በመንገዱ ሲናገረን፣ መጻሕፍትን ሲተረጉምልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን» ከዚያም ወደ ኢየሩሌም ተመለሱ።

እነዚህ ሰዎች ጌታችን መጻሕፍትን ሲያስተምራቸው ይሰማቸው የነበረውን ነገር የገለጹበት «ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን» የሚለው አባባልና ከዚያም ከተስፋ መቁረጣቸው ተጽናንተው ወደ ኢየሩሳሌም መመለሳቸው ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሰሚቸውንና የሚያነቧቸውን ሰዎች ልብ ለመግዛትና ወደ ትክክለኛው /የቅድስና/ መንገድ ለመምራት ያላቸውን ኃይል ያሳያል።

በንጉሡ በኢዮስያስ ዘመንም ጠፍቶ የነበረው የሕግ መጽሐፍ /ኦሪት ዘዳግም/ ተገኝቶ በተነበበ ጊዜ የሆነው ነገር በሁለተኛው መጽሐፈ ነገሥት እንደሚከተለው ተመዝግቧል፤

«ንጉሡም የሕጉን መጽሐፍ ቃል በሰማ ጊዜ ልብሱን ቀደደ፣ «አባቶቻችን በእርስዋ የተጻፈውን ሁሉ ይጠሩ ዘንድ የዚችን መጽሐፍ ቃል ስላልሰሙ በላያችን የነደደው የእግዚአብሔር ቁጣ ብዙ ነው» . . . አለ»

ከዚያም በእግዚአብሔር ቤት የተገኘውን የቃል ኪዳኑን መጽሐፍ ቃል በሕዝቡ ሁሉ ጆሮ አነበበ:: . . . ንጉሡም እግዚአብሔርን ተከትሎ ይሄድ ዘንድ ትእዛዙንና ምሥጢሩንም ሥርዓቱንም በፍፁም ልቡና በፍፁም ነፍሱ ይጠብቅ ዘንድ በዚሁም መጽሐፍ የተጻፈውን የቃል ኪዳን ቃል ያጸና ዘንድ ቃል ኪዳን አደረገ፤ ሕዝቡም ሁሉ ቃል ኪዳን ገቡ::» /፪ነገ. ፳፫÷፩-፫፣፪ነገ. ፳፪÷፰-፲፫/

ይህም ታሪክ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ሰዎች ስለ ኃጢአታቸው እንዲጸጸቱና ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ለማድረግ ያላቸውን ኃይል የሚያመለክት ነው::

በሕይወታቸው እግዚአብሔርን ካስደሰቱና እኛም ለመንገዳችን አርአያ ልናደርጋቸው ከሚገቡ ቅዱሳን መካከል ብዙዎቹ ጥልቅ የቅዱሳት መጻሕፍት እውቀት የነበራቸው መሆኑ ይህንን አባባል ያጠናክራል::

የክርስቶስን አምላክነት በመመስከሩ ምክንያት አይሁድ በድንጋይ እየወገሩት ሳለ ሰማየት ተከፍተውለት ጌታችንን በአብ ቀኝ ሆኖ /ምስጢረ ሥላሴን/ የተመለከተው ቅዱስ እስጢፋኖስ /ሐዋ. ፯÷፶፭/ ጥልቅ የቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀት ነበረው:: «ይናገርበት የነበረውን መንፈስና ጥበብ ይቃወሙ ዘንድ አልተቻላቸውም» /ሐዋ. ፮÷፲/

ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም በዘመኑ ከነበረው ታዋቂ የህግ /የኦሪት/ መምህር ከገማልያል እግር ሥር ቁጭ ብሎ ቅዱሳት መጻሕፍትን የተማረ ሰው ነው:: /ሐዋ.22÷3/

በኋላ ዘመን የተነሱና ቅድስናቸው የተመሰከረላቸው እነ ቅዱስ አትናቴዎስ ቅዱስ ኤፍሬም፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ እና የመሳሰሉት አባቶችም ጥልቅ የቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀት ነበራቸው::

## 1.4 የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሞች

የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅሞች በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍለን ልናያቸው እንችላለን::

**ሀ. እግዚአብሔርን ለማወቅ**

ሰው በተፈጥሮ ዕውቀቱ በመጠቀምና በመመራመር የፈጣሪውን መኖር ወደ ማወቅና ወደ ማመን ሊደርስ ይችላል:: እግዚአብሔር በእያንዳንዳችን ውስጥ ያስቀመጠ ውን የአምልኮ /የሃይማኖት/ ዝንባሌ በማዳመጥ እና ውብ ሆኖና በሥርዓት እንዲኖር ተደርጎ የተፈጠረውን ሥነ ፍጥረት በመመልከት፣ ታሪክንም በማጥናት ለዚህ ዓለም ፈጣሪ፣ ሠራኢ፣ መጋቢ፣ ተቆጣጣሪ እንዳለው ማወቅና ማመንም ይቻላል:: በተለያዩ ዘመናት የተነሡ የተለያዩ ፈላስፎችም በዚህ መልኩ በምርምር የአንድ ፈጣሪን መኖር አውቀው አምነዋል፤ አስተምረዋልም::

ይሁን እንጂ ትክክለኛው የእግዚአብሔር ማንነትና ባሕርይ እንዲሁም የሰው ልጆችን ለማዳን ያደረገውን ጉዞ ሙሉ በሙሉ መረዳት የሚቻለው በሰው ልጆች በልቡና ምርምር ሳይሆን በእግዚአብሔር ራሱን መግለጥ ነው::

ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን ሰዎች በጻፈው መልእክት መግቢያ ላይ «ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ተናገረን::» /ዕብ.1፥1/ እንዳለው እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ ለሰው ልጆች ራሱን፣ ማንነቱንና ባሕርዩን እንዲሁም የሰው ልጆች ለማዳን ያለውን ዕቅድ ቀስ በቀስ በተለያዩ መንገዶች ገልጧል:: በመጨረሻም ደግሞ ሰው ሁኖ በተወለደው ልጁ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት የበለጠ ማንነቱን እንድናውቅ አድርጎናል:

እንግዲህ በእነዚህ የእግዚአብሔር መገለጥ በተደረጉባቸው ዘመናት በአካለ ሥጋ የነበሩ ሰዎች መገለጡን በዓይናቸው አይተው፣ በጆሮአቸው ሰምተው በእጃቸውም ዳሰው

የመገለጡ ተጠቃሚ ሆነዋል። እርሱ የፈቀደላቸውን ያህልም እግዚአብሔርን አውቀውታል።

ዛሬ በዚህ ዘመን ያለን ሰዎች በራሱ መገለጥ የታወቀውን የእግዚአብሔር ማንነትና ባሕርይ ለማወቅ የግዴታ በእነዚያ ዘመናት የተደረጉትን መገለጦች ማወቅ አለብን። ይህንን ካላወቅን ስለ አምላካችን ያለን ዕውቀት በልቡና ምርምር ሊታወቅ የሚችለውን ያህል ብቻ ይሆናል። ይህ ደግሞ ፍፁምና በቂ አይሆንም። ስለዚህ በተለያዩ ዘመናት የተደረጉትን መገለጦቹ የተመዘገቡባቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት መጠቀም የግድ ይሆንብናል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሌላው ቅዱሳት መጻሕፍትን የማንበብ፣ የመረዳትና የማወቅ ጥቅም የምናምነውን አምላካችንን በትክክል ለማወቅ ነው። ዛሬ በዓለማችን ያሉ በክርስትና ስም እንኳን የሚጠሩና እኛ የያዝነውን መጽሐፍ ቅዱስ የያዙ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ክፍሎች አሉ። ለእነዚህ ሁሉ መፈጠር ዋናው ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስን በተለያየ መልኩ መተርጎም፣ መረዳትና በዚህም ምክንያት «አምላካችን ማን ነው? ባሕርይውስ?» በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ የተለያየ ግንዛቤ መያዝ ነው።

ስለዚህ በትክክለኛው የእምነት ጎዳና ለመገኘትና በዚያም ለመጽናት ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብና አምላካችንን እርሱ የወደደውና የፈቀደልንን ያህል መረዳት የግድ ነው።

«እንግዲህ ያላመኑበትንስ እንዴት አድርገው፤ ይጠሩታል፤ ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ ... እምነት ከመስማት ነው፤ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው» /ሮሜ. 10፥14-17/

**ለ. የሕይወት መመሪያ ነው**

መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሰው በራሱ ሊመልሳቸው ለማይችላቸው ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል።

1. ከየት መጣሁ? ለምንስ መጣሁ?
2. ወደ የትስ እሄዳለሁ?

ለእነዚህ ሁለት ጥያቄዎች መልስ ከሰጠ በኋላ ከዚህ በመነሳት ለሌላ ሦስተኛ ጥያቄ መልስ ይሰጣል።

3. አሁን ምን እያደረግሁ ነው? ምን መሆንና ምን ማድረግ ይጠበቅብኛል? እንዴትስ ይህንን የሚጠበቅብኝን መሆንና ማድረግ እችላለሁ?

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ማንነታችን እንድንረዳና መሆንና ማድረግ የሚጠ በቅብንን እንድናውቅ የሚረዳ የሕይወት መመሪያ፣ ልንጓዝበት የሚገባንን መንገድ የሚያሳይ የሕይወት ካርታ ነው።

### ሐ. የአገልግሎት መመሪያ ነው

አገልግሎት የሚለው ቃል ሁለት ጉዳዮችን ሲወክል ይችላል፡-

1. ለፈጠረን፣ለሚጠብቀንና ለሚመግበን በድለን ስንወድቅ የሞት ዋጋ ከፍሎ ላዳነን አምላካችን አምልኮና ምስጋና፣ እርሱ ለመረጣቸው ቅዱሳን ደግሞ አክብሮትና ምስጋና የምናቀርብባቸው ሂደቶች አገልግሎት ይባላሉ። /ጸሎት፣ቅዳሴ፣ስግደት. ./

2. እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ የማያመልኩትንና ልጁን ወደዚህ ምድር ልኮ የጠፋውን ዓለም ማዳኑን ያላመኑንና ያልተቀበሉትን አስተምሮ ወደ ትክክለኛው እምነት /ሃይማኖት/ ለማምጣትና በሃይማኖት ያሉትም እግዚአብሔርን የሚያስደስት ኑሮ እንዲኖሩ ለማድረግ የሚሠሩ ሥራዎች አገልግሎት ይባላሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ሁለቱንም አገልግሎቶች ለምን እንደምናገለግል፣ እንዴት ማገልገል እንዳለብን እና የአገልግሎት ዋጋችን ምን እንደሆነ ስለሚነገረን የአገልግሎት መመሪያ ነው።

### መ. ለምድራዊ ሕይወታችን መሳካት

የሰው ልጅ ወደማያልፈው ዓለም ከመሸጋገሩ በፊት በዚህ ዓለም ጥቂት የዝግጅት ዘመናትን ያሳልፋል። መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጅ በዚህ ዓለም ሲኖር ለማያልፈው ዓለም ለሚያደርገው ዝግጅት ብቻ ሳይሆን በዚህ ዓለም የሚኖረው ኑሮ ስኬታማ እንዲሆን በርካታ ጥቅሞችን ይሰጣል። ለማሳያ እንዲሆን ሁለት ነገሮችን እንጥቀስ።

- ሰዎች ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ተከትለው ቢኖሩ ዓለማችን ፍትሕ፣ ነጻነት፣ እኩልነት፣ ፍቅር የሰፈነባት ስጋት የጠፋበት ጥሩ የመኖሪያ ስፍራ ትሆን ነበር።

➢ *መጽሐፍ ቅዱስ የምድራዊ ጥበብ ምንጭ ነው፡ ስለ ዓለም ታሪክ፣ ሕግና አስተዳደር፣ ሕክምና፣ ግንባታና ስነ ሕንፃ፣ ወዘተ በርካታ ቁም ነገሮችን ያስተምረናል።*

በአጠቃላይ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከማንበብና ከማወቅ እነዚህና ሌሎች በርካታ ጥቅሞች ይገኛሉ። መጻሕፍትን አለማወቅ ደግም «ህዝቤ ዕውቀት በማጣት ጠፋ» /ሆሴ 4÷6/ እንተባለው የጥፋት መንገድ ነው። ስለዚህ በቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት ልንበረታ ይገባናል። ሐዋርያውም «የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ» /ቆላ. 3÷16/ እያለ የሚመክረን ለዚሁ ነው።

## 1.5. **የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መርሆዎች**

ቅዱሳት መጻሕፍትን ስናጠና ልንረዳቸውና ሁል ጊዜም ልናስተውላቸው የሚገቡ ሁለት መሠረታዊ መርሆዎች አሉ እነዚህም።

**ሀ. ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ፣ ማጥናትና መረዳት ማለት የጽሑፉን ትርጉምና እግዚአብሔር በዚያ ጽሑፍ አማካኝነት ለእኛ እያስተላለፉ ያሉትን መልእክት በትክክል መረዳት ማለት ነው።**

**ቅዱሳት መጻሕፍት ደግሞ የተጻፉት በእግዚአብሔር መሪነት በመሆኑ በመጻሕፍቱ ባለቤት ፈቃድና ዕርዳታ ካልሆነ በስተቀር ይህንን ማድረግ አይቻልም። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን እንዲህ በማለት በግልጽ ተናግሮታል፡-**

«ከእናንተ ጋር ስኖር ይህን ነግሬአችኋለሁ አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፤ እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።»/ዮሐ.14÷25-26/

«የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም። ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል።» /ዮሐ.16÷12-13/

ቅዱስ ጳውሎስም ለቆሮንቶስ ምእመናን ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ በማለት ጽፎላቸዋል፡-
«በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን በጥበብዋ ስላላወቀች በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃዱ ሆኗል።» /1ኛ ቆሮ.1÷21/
«መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ይመረምራልና፣ ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው።» /1ቆሮ.2÷10/

በአጠቃላይ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብም ሆነ መረዳት የሚቻለው በመጻሕፍቱ ባለቤት በእግዚአብሔር ፈቃድና እርዳታ ነው።

ለ. **ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብና ትርጉማቸውን መረዳት የክርስቲያኖች ግብ አይደለም። ግባችን ያወቅነውን መፈፀምና በተረዳነው መጠን መኖር ነው። የቅዱሳት መጻሕፍትን ጥናት ወደዚህ የሚያመጣ መንገድ ብቻ ነው።**

ጌታ ቃለ እግዚአብሔርን እንዴት መማር እንዳለብን በዘር፣ በምድር ፣ በፍሬ በመሳሰሉት መስሎ እንዲህ በማለት አስተምሯል።

«እነሆ ዘሪ ሊዘራ ወጣ። እርሱም ሲዘራ አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ፣ ወፎችም መጥተው በሉት። ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀ ፤ ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፣ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፣ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ። ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፣ እሾህም ወጣና አነቀው። ሌላውም በመልካም መሬት ላይ ወደቀ፣ አንዱም መቶ አንዱም ስድሳ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።» /ማቴ.13፥1-9/

ደቀመዛሙርቱ ምሳሌውን እንዲተረጉምላቸው ሲጠይቁትም አራቱ ዓይነት የዘር አወዳደቆች የአራት ዓይነት ሰዎች ምሳሌ መሆኑን አስረድቷቸዋል። /ማቴ.13፥18፥23/። እነዚህም፡-

1. መንገድ ዳር በወደቀው ዘር የተመሰሉት ቃሉን የሚማሩ ግን የማያስተውሉ /የማይረዱ/ ናቸው
2. በጭንጫ ላይ በወደቀው ዘር የተመሰሉት ቃሉን የሚማሩ የሚረዱና ለጊዜው የሚቀበሉ፤ ነገር ግን በቀላል መከራ ሳይቀር እየተሸነፉ የማይፈጽሙት ናቸው።
3. በእሾህ መካከል በወደቀው ዘር የተመሰሉት ቃሉን የሚማሩ የሚረዱና የሚቀበሉ ነገር ግን ምድራዊ ሕይወታቸው እያደሉና ይህ ማነቆ እየሆነባቸው የማይፈጽሙት ናቸው።
4. በመልካም መሬት ላይ በወደቀው ዘር የተመሰሉት ቃሉን የሚማሩ፣ የሚረዱና የሚቀበሉ፣ በዚያም መሠረት የሚኖሩ ናቸው።

በዚህ ምሳሌ ላይ ቃለ እግዚአብሔርን እየተማሩ /እየሰሙ፣ እያነበቡት/ አለማስተዋል /አለመረዳት፣ችላ ማለት/ ብቻ ሳይሆን በተግባር እስካልፈጸሙት ድረስ መረዳትና መቀበል ብቻውን በቂ እንዳልሆነ በግልጽ ተቀምጧል።

ቅዱስ ያዕቆብም ይህንን በተመለከተ በመልእክቱ እንዲህ ይላል፤ «ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ። ቃሉን የሚሰማ የማያደርገውም ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስተዋት የሚያይ ሰውን ይመስላል። ራሱን ዐይቶ ይሄዳልና፣ ወዲያውም እንደ ምን እንደሆነ ይረሳል። ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው በሥራው የተባረከ ይሆናል።»/ያዕ.1÷22 -25/

ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍትን ስናነብ ዓላማችን ሊሆን የሚገባው መጻሕፍቱን በማንበብ የእግዚአብሔርን ፈቃድና ዓላማ ተረድተን እንደ እርሱ ፈቃድ መኖርና እርሱን ማስደሰት ነው።

እነዚህን ሁለት መርሆዎች ከተረዳን በኋላ ቀጥለን «እነዚህን መርሆዎች ጠብቀን ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማንበብ ምን ማድረግ አለብን?» ወደሚለው እንሄዳለን።

## 1.6. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መመሪያዎች

### 1.6.1. ዝግጅት ማድረግ

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለማድረግ ስንነሣ ማድረግ ያለብን ሦስት ዋና ዋና ዝግጅቶች አሉ። እነዚህም፡-

#### *ሀ. ጸሎት*

ጸሎት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር፤ ማመስገን፣ ልመና ማቅረብ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ልናነብ ስንነሣ የመጻሕፍቱ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር እንድናነባቸውና እንድናጠናቸው ቅዱስ ፈቃዱ እንዲሆንልን፣ ትክክለኛ ትርጉምና መልእክታቸውን እንድንረዳ እንዲያግዘን ማወቅና መረዳት ብቻ ሳይሆንም ያወቅነውንም እንድንኖርበት እንዲረዳን መለመን፤ ስለሚያደርግልንም ነገር ሁሉ ማመስገን አለብን።

ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶንና ለቆላስይስ ሰዎች በጻፋቸው መልእክታቱ እንዲህ ይላል፡-

- «የወንጌልን ምሥጢር በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ስለ እኔ ለምኑ።» /ኤፌ.6÷19/።
- «እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍታልኝ ዘንድ ስለ እኛ ደግሞ ጸልዩ።» /ቆላ.4÷3/

ሐዋርያው የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጉምና መልእክት ይረዳ ዘንድ፣ ደጃቸውም ይከፈትለት ዘንድ ራሱ መጸለይ ብቻ ሳይሆን ሌሎች እንዲጸልዩለትም መጠየቁ ለቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት ጸሎት አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳናል፡፡

ቅዱስ ያዕቆብም «ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፤ ለእርሱም ይሰጠዋል» በማለት ይመክረናል፡፡ /ያዕ.1÷7/

ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከማንበባችንና ከማጥናታችን በፊት ልቡናችንን ብሩህ እንዲያደርግልንና ትክክለኛ ትርጉምና መልእክታቸውን እንድንረዳ እንዲያደርገን፤ እያነበብን ሳለን ደግሞ ለመረዳት ከባድ የሆነ ነገር ሲያጋጥመን የተሰወረውን እንዲገልጥልን፣ አንብበን ከጨረስን በኋላም ያነበብነውንና የተረዳነውን በልቡናችን እንዲያሳድርልንና በሕይወት እንድንኖረው እንዲረዳን እግዚአብሔርን መለመን አስፈላጊ ነው፤ ስለሚያደርግልን ነገር ማመስገንም እንዲሁ፡፡

### ለ. ቦታ እና ጊዜ ማዘጋጀት

በቅዱሳት መጻሕፍት ጥናት ውጤታማ ለመሆን ለጥናቱ የሚመች ቦታ እና ጊዜ መምረጥና ማዘጋጀት /መመደብ/ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

የሚመረጠው ቦታ በተቻለ መጠን ኅሊናን የሚሰርቁ እና ከመንፈሳዊ ሐሳብና ስሜት የሚያርቁ ነገሮች የሌሉበት ቢሆን ይመረጣል፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍትን በዘፈቀደ በተለያየ ሰዓት ከማጥናት ይልቅ የተወሰነ ጊዜ መድቦና ያንን ጊዜ ጠብቆ ማጥናት ወጥነት ባለው መልኩ ጥናቱን ለማካሔድ ያስችላል፡፡[1] ይህ ማለት ግን በምናገኘው አጋጣሚና በተመቸን ቦታ ሁሉ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ የለብንም ማለት አይደለም፡፡

### ሐ. ለጥናት የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ማዘጋጀት

በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ስኬታማ ለመሆን ልናደርገው የሚገባው ሌላው ዝግጅት ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን በተቻለ መጠን ማዘጋጀት ነው፡፡ እነዚህም ትክክለኛ ትርጉም ያለው መጽሐፍ ቅዱስ[2]፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ የታሪክ

---

[1] መጽሐፍ ቅዱስን ማታ ከማጥናት ይልቅ ህሊና ንቁ በሚሆንበት ጊዜ በጠዋት ተነሥቶ ማጥናት የተሻለ እንደሆነ መምህራን ይመክራሉ፡፡

2 በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች /ከቋንቋ ወደ ቋንቋ/ /translations/ አሉ፡፡ በክፍል ሦስት በዝርዝር እናያቸዋለን፡፡

መጻሕፍት፣ ካርታዎች፣ ማስታወሻ ደብተሮች እና የመሳሰሉት ናቸው:: ቀሪዎቹን እና የእያንዳንዳቸውን አስፈላጊነትና አጠቃቀም ወደፊት በሚመጡት ምዕራፎች እንመለከታለን::

### 1.6.2. በመገዛት፣ በማድነቅ እና በትሕትና ማንበብ

ቅዱሳት መጻሕፍትን ስናነብ በመጻሕፍቱ ባሉት ቃላት አማካኝነት እየተናገረን ያለው እግዚአብሔር እንደሆነ ማስተዋልና ለምናነበው ነገር ለመገዛት ልባችንን መክፈት አለብን::

በመጻሕፍቱ ያሉትን የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራዎች /ተአምራት፣ የአምላክን ሰው መሆን፣ የሥላሴን /የአምላክን አንድነትና ሦስትነትን ነገር እና የመሳሰሉትን/ ስናነብ ትኩረታችን ጉዳዮቹን መተንተንና እንዴት እንደሆኑ ማብራራት ከመሆን ይልቅ የሆኑትን ነገሮችን ማድነቅ ሊሆን ይገባዋል:: የበለጠም ተጠቃሚ ያደርገናል:: ምክንያቱም የማይወሰነውን እግዚአብሔርን እና ሥራዎቹን ውሱን በሆነው የሰው ልጅ አእምሮ አስቡ ሙሉ በሙሉ መረዳት ስለማይቻል ነው:: ቅዱስ ጳዉሎስም «እንደ ባለ አዕምሮ እንጂ ማሰብ ከሚገባችሁ አልፋችሁ እንዳትመራመሩ እመክራለሁ» / / በማለት የመረዳት ጥረታችንንና አቅማችንን ያገናዘበ እንዲሆን ይመክራል:: ስለዚህም የሆኑትን ነገሮች ከመተንተን እና ከማብራራት ይልቅ ለእምነታችን መጠንከር አስተዋጽኦ የሚያደርገው እግዚአብሔር የማይቻለው እንዲቻል እንዳደረገ አስተውሎ ሁሉን ቻይነቱንና ገናናነቱን ማድነቅ ነው:: ድንቅ ሥራዎቹ የተደረጉበትና የተጻፈበት ምክንያትም ይኸው ነው::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ እግዚአብሔር ቀስ በቀስ በዘመናት የሚገልጠው ምስጢር እንዳለ መገንዘብና «ሁሉን በአንድ ጊዜ መረዳት አለብኝ» ከሚል ስሜት መራቅም ያስፈልጋል:: ነቢዩ ዳንኤል በእግዚአብሔር ዕርዳታ ብዙ ህልሞችን ካየና ከተረጎመ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ «ጥበብ ልጨምርልህ መጥቻለሁ» /ዳን. / ብሎታል:: ይህም ጥበብን እግዚአብሔር ቀስ በቀስ ለሰዎች እንደሚሰጥ ያሳየናል::

ጌታም ለሐዋርያት በርካታ ነገሮችን ከነገራቸው በኋላ «የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፥ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም:: ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል::» /ዮሐ.16፥12/:: ብሏቸዋል:: ይህም እግዚአብሔር ቀስ በቀስ ለሰው ልጆች እንደሚሰጥና እንደሚገልጥ የሚያመለክት ነው::

ስለዚህ በጥናታችን ወቅት የማይገባንና ለመረዳት የሚከብደን ነገር ሲያጋጥመን እግዚአብሔር እንዲገልጥልን በጸሎት ጠይቀን ማለፍንና ፈቃዱ ሆኖ ያንን ነገር እንድንረዳው የሚያደርግበትን ቀን በትእግሥትና በእምነት መጠበቅ አስፈላጊ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የኢሳይያስን መጽሐፍ እያነበበ ሳለ ቅዱስ ፍሊጶስ «የምታነበውን ታስተውለዋለህን?» ሲለው «የሚመራኝ ሳይኖር እንዴት ይቻለኛል?» ብሎ በትሕትና እንዲያስረዳው እንደለመነው /ሐዋ.8÷30-31/ እኛም በትሕትና ወደ መምህራን መቅረብና ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲያብራሩልንና እንዲተረጉሙልን መጠየቅ የቤተክርስቲያን አባቶችና መምህራን ያዘጋጇቸውን የትርጓሜ እና የማብራሪያ መጻሕፍት መጠቀምም ይኖርብናል።

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው ነገሮች ሁሉ ከመንፈሳዊነት ማደግ ጋር አብረው የሚያድጉ ናቸው። ስለዚህ ለዚህ በሚያበቁ ነገሮች ማለትም በጸሎት፣ በጾም፣ በተመስጦ፣ በስግደት ልንበረታ ይገባናል።

### 1.6.3. የምናነበውን ነገር ትርጉምና እግዚአብሔር በዚያ ጽሑፍ አማካኝነት እያስተላለፈ ያለውን መልእክት በትክክል ለመረዳት መጣር

አስቀድመን እንደተናገርነው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዓላማ የምናነበውን ነገር ትክክለኛ ትርጉም እንዲሁም እግዚአብሔር በዚያ ጽሑፍ አማካኝነት እያስተላለፈ ያለውን መልእክት በትክክል መረዳት ነው።

ቋንቋ እና ጽሑፍ ሐሳብን የማስተላለፊያ መንገዶች ናቸው። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ አንድን ጽሑፍ በምናነብበት ጊዜ ትርጉሙን ለመረዳት ሊከብደን ወይም ለትርጉም አሻሚ የሆነ ንባብ ሊያጋጥመን ይችላል። ከዚህም በተጨማሪ ጽሑፉን እግዚአብሔር /ወይም ጸሐፊው/ እንዲኖረው ካሰበው በተለየ መንገድ ልንረዳውም እንችላለን።

በእርግጥ እነዚህን ችግሮች አስወግዶ መጻሕፍትን እንድንረዳ የሚያደርገው እግዚአብሔር ነው። ነገር ግን ከእኛ የሚጠበቁና ልናደርጋቸው የሚገቡ ነገሮች አሉ።

#### ሀ. የመጽሐፉንና የጸሐፊውን ዳራ መረዳት

ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት ከረጅም ጊዜ በፊት /ቢያንስ ከ3500 ዓመታት በፊት/ ነው። ስለዚህ መጻሕፍቱ በተጻፉበት ዘመን የነበረው ሁኔታ ማለትም ባህል፣

ቋንቋና አነጋገር፣ መልክአ ምድር፣ ሥልጣኔና ጥበብ፣ ወዘተ አሁን ካለው በብዙ መልኩ የተለየ ነው፡፡ መጻሕፍቱ የተጻፉበት ቦታ እኛ ዛሬ ካለንበት ቦታ የተለየ ሲሆን ደግሞ ልዩነቱ የበለጠ ይሰፋል፡፡

መጻሕፍቱን ልንረዳቸው የሚገባው በዚያው በተጻፉበት ዘመን እና ቦታ ከነበረው ሁኔታ አንጻር እንጂ ዛሬ ካሉት ሁኔታዎች /ቋንቋ፣ ባህል፣ .../ ባለመሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመረዳት እነዚህን ነገሮች ማጥናት አስፈላጊ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የጸሐፊውን ማንነት፣ ጽሑፉ የተጻፈበትን ዓላማ፣ ወዘተ/ ማጥናትና መረዳት ለጥናታችን ውጤታማነት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህን ጉዳዮች በዝርዝር በክፍል ዐራት እንመለከታቸዋለን፡፡

**ለ. ዐውደዊ ፍቺ መጠቀም**

ቅዱሳት መጻሕፍትን ስናነብብና ስንተረጉም እያንዳንዷን ቃል ልንፈታት የሚገባን በዚያው ባለችበት ዓረፍተ ነገር ውስጥ ካላት ድርሻ አንጻር መሆን አለበት፡፡ ዓረፍተ ነገሩንም እንዲሁ ባለበት ምዕራፍ ውስጥ ካለው ድርሻ አንጻር፣ ምዕራፉንም ከጠቅላላው ከመጽሐፉ ይዘትና ዓላማ አንጻር መተርጎምና ለመረዳት መሞከር አለብን፡፡

**ሐ. ጉዳዮችን በአጠቃላይ ዕይታ መረዳት**

አንድን ጉዳይ /እውነት/ በትክክልና በጥልቀት ልንረዳው የምንችለው ጉዳዩን ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንጻር ስንመረምረው፣ በጉዳዩ ላይ የተባሉ ነገሮችን በሙሉ ስንዳስስና ጉዳዩን በምልአት ስናውቀው ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን ስናጠናም ይህንኑ ማድረግ አለብን፡፡ ስለዚህ አንድን ጉዳይ በተመለከተ /ለምሳሌ ድኅነት፣ ጸሎት፣ እምነት፣ ፍርድ፣ ምልጃ፣ .../ ቅዱሳት መጻሕፍትን ስናነብ በጉዳዩ ላይ አንድ ንባብ ወይም መጽሐፍ የሚለውን ብቻ ሳይሆን ስለ ጉዳዩ በተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት የተባሉትን ነገሮች ሁሉ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡

ይህ ሲደረግ በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያዩ /የሚቃረኑ/ የሚመስሉ ሐሳቦች ከተለያዩ ቦታዎች ሊገኙ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ ትምህርት ከምን አንጻር እንደተሰጠ ስናጠና ቀስ በቀስ በጉዳዩ ላይ ከጽንፈኝነት እና ከከፊል እይታ የራቀ የተሟላ ዕውቀትና መረዳት ይኖረናል፡፡

**መ. ተገቢውን ቅደም ተከተል ጠብቆ ማንበብ**

ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ መግቢያ ላይ «ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ÷ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ... በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን» /ዕብ.1÷1/ እንዳለው የእግዚአብሔር ለሰው ልጆች መገለጥ ቀስ በቀስና ደረጃ በደረጃ የተደረገ ነው:: በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ የተደረገው መገለጥም ከዚያ በፊት የነበረውን መገለጥ መሠረት ያደረገ ነው:: እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ወደዚህ ዓለም ልኮ ዓለሙን ያዳነበት መንገድ ከዚያ በፊት በነበሩ ዘመናት የተደረጉ ዝግጅቶችን መሠረት ያደረገ ነው:: ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍትን ስናጠና በዘፈቀደ ወይም መጽሐፍ ቅዱሱን ስንከፍት ያገኘነውን ነገር ከማንበብና ከማጥናት ይልቅ ትክክለኛውን ቅደም ተከተል ተከትሎ መጻሕፍቱን ማንበብ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖረን ያደርጋል:: ቅዱሳት መጻሕፍቱ እንዴት ባለ ቅደም ተከተል ቢጠኑ ይሻላል የሚለውን ወደፊት እንመለከታለን::

### 1.6.4. ለሕይወት ማንበብ

ቅዱሳት መጻሕፍትን የምናጠናበት ዓላማ የእግዚአብሔርን ማንነት፣ ራሳችንን፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን መልካም ዕቅድ እና ለዚህ ዕቅድ መሳካት ከእኛ የሚጠበቀውን ተረድተን የሚጠበቅብንን ለማድረግ መሆኑን ተመልክተናል::

ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍትን ስናጠና ይህንን ልብ ማለትና ለማስተማርና ለመጻፍ ከማንበብ በፊት በመጻሕፍቱ መስተዋት ራስን እየተመለከቱ ማንበብና ማጥናት የግድ ነው:: ይህም ማለት የእግዚአብሔርን ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅር፣ ቸርነት፣ ረዳትነት መገንዘብና ማጣጣም፣ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን እቅድ ከተረዳን በኋላ ራሳችንን ከዚያ አንጻር መገምገምና የሚጎድለንን መረዳት፣ መንገዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ካደረጉ ቅዱሳንና በጥፋታቸው ከወደቁ ሰዎች የሕይወት ተሞክሮ ትምህርት በመወሰድ መጻሕፍትን ማጥናት ማለት ነው::

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በአግባቡ ካልተያዘና ካልተጠቀሙበት በርካታ ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል:: ቅዱስ ጳውሎስ «እውቀት ያስታብያል» በማለት እንደገለጸው /1ኛቆሮ.8÷1/ ብዙ ማወቅ ትዕቢት ሊያስከትል ይችላል:: ቅዱስ ያዕቆብም «ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ» /ያዕ.1÷21/:: በማለት የመከረን ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበባችንና በመረዳታችን ብቻ ወደ እግዚአብሔር የቀረበን ሊመስለን፣ ያወቅነውንም ዕውቀት ለራሳችን መመሪያ ከማድረግ

ይልቅ ሌሎችን መውቀሻ ልናደርገውና ልንሰናከልበት ለምንችል ከዚህ እንድንታቀብ ነው፡፡

ስለዚህ ዘወትር ራሳችንን መፈተሽና መመርመር እንዲሁም ከእነዚህና ከሌሎች ብዙ እኛ ከማናውቃቸውና ከማናስተውላቸው ችግሮች ጠብቆ የቅዱሳት መጻሕፍት ጥናታችንን ለሕይወት እንዲያደርግልን እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅ አለብን፡፡

***ይቆየን፡፡***